# ቤተክርስቲያን

## የሐዋሪያ ሥራ  የቡድን ጥናት መመሪያ

<u>**የሐዋሪያ ሥራ ጥናት**</u>

1. አንደኛ ሣምንት፣ ለክርስቶስ ምስክር መሆን፣ ሐዋ:1:1-15 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣1:8)
2. ሁለተኛ ሣምንት፣ ለክርስቶስ ምስክር መሆን፣ ሐዋ:1:1-11 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣1:8)
3. ሦስተኛ ሣምንት ፣ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ፣ ሐዋ:2:1-24 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣1:8)
4. አራተኛ ሣምንት፣ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል መዘጋጀት፣ ሐዋ፣2:36-41 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣1:8)
5. <u>አምስተኛ ሣምንት ፣ የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>
6. ስድስተኛ ሣምንት ፣ በቃሉ መኖር ፣ሐዋ፣2:42-47 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣2:38-39)
7. ሰባተኛ ሣምንት ፣የተአምራት ምስክርነት ፣ሐዋ፣3:1-19 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣2:38-39)
8. ስምተኛ ሣምንት ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለኢየሱስ ቆራጥ ምስክሮች ነበሩ ፣ ሐዋ፣4:1-31 (የቃልጥናት፡- ሐዋ፣2:38-39)
9. ዘጠነኛ ሣምንት ፣ በታማኝነት በመኖር ምስክር መሆን ፣ሐዋ፣4:32-5:11 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣2:38-39)
10. <u>አሥረኛ ሣምንት ፣ የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>
11. አሥራ አንደኛ ሣምንት ፣የአገልግሎት ምስክርነት ፣ ሐዋ:6:1-7 (የቃል ጥናት፡-ሮሜ፣12:4-5)
12. አሥራ ሁለተኛ ሣምንት ፣ የአገልግሎት ምስክርነት፣ኤፌ:6:5-8 (የቃል ጥናት፡-ሮሜ፣12:4-5)
13. አሥራ ሦስተኛ ሣምንት ፣ መስዋዕት በመሆን መመስከር ፣ሐዋ፣7 (የቃል ጥናት፡-ሮሜ፣12:4-5)
14. አሥራ አራተኛ ሣምንት ፣ የመስካሪ ግዴታ ፣ሐዋ፣8:26-40 (የቃል ጥናት፡-ሮሜ፣12:4-5)
15. <u>አሥራ አምስተኛ ሣምንት ፣ የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>
16. አሥራ ስድስተኛ ሣምንት ፣የመታዘዝ ምስክርነት ፣ሐዋ፣9:1-19 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣11:18)
17. አሥራ ሰባተኛ ሣምንት ፣የተለወጠ ሕይወት ምስክርነት ፣ሐዋ፣9:20-31 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣11:18)
18. አሥራ ስምንተኛ ሣምንት ፣ ጥላቻን የማሸነፍ ምስክርነት፣ ሐዋ፣10:1-29፣34-35 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣11:18)
19. አሥራ ዘጠነኛ ሣምንት ፣የቤተክርስቲያን አገልግሎት ፣2ቆሮ:5:14-21 (የቃል ጥናት፡-ሐዋ፣11:18)
20. <u>ሃያኛ ሣምንት ፣የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>
21. ሃያ አንደኛ ሣምንት ፣ጴጥሮስ ከእሥር ቤት ወጣ ፣ሐዋ:12:1-19 (የቃል ጥናት፡-ኤፌ:4:15-16)
22. ሃያ ሁለተኛ ሣምንት ፣ለጌታ የተሰጠ ሕይወት ፣ሐዋ፣12:25-13:5 (የቃል ጥናት፡-ኤፌ:4:15-16)
23. ሃያ ሦስተኛ ሣምንት ፣የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ፣ሐዋ፣12:25-13:5 (የቃል ጥናት፡-ኤፌ:4:15-16)
24. ሃያ አራተኛ ሣምንት ፣ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ምስክርነት፣1ቆሮ:12:12-27 (የቃል ጥናት፡-ኤፌ:4:15-16)
25. <u>ሃያ አምስተኛ ሣምንት ፣ የፀሎትና የአንድነት ጊዜ</u>
26. ሃያ ስድስተኛ ሣምንት፣የሚስዮናዊያን (የወንጌል መልክተኞች) ምስክርነት ፣ሐዋ:14:1-7 (የቃል ጥናት፡-ሮሜ:12:18)
27. ሃያ ሰባተኛ ሣምንት ፣አርነት ፣ሐዋ:15:1-29 (የቃል ጥናት፡-ሮሜ:12:18)
28. ሃያ ስምንተኛ ሣምንት ፣በመስካሪዎች መካከል የተነሳው ክርክር፣ ሐዋ፣15:36-16:5 (የቃል ጥናት፡-ሮሜ:12:18)
29. ሃያ ዘጠነኛ ሣምንት ፣የእግዚአብሔር ቤተሰብ፣1ጢሞ፣3:1-15 (የቃል ጥናት፡-ሮሜ:12:18)
30. <u>ሰላሣኛ ሣምንት፣የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>

31. ሰላሣ አንደኛ ሣምንት፣ የችግር ጊዜ፣ ሐዋ፣16፡16-34 (የቃል ጥናት፦ፍልጵ፡4፡12-13)
32. ሰላሣ ሁለተኛ ሣምንት፣ የእውነት ምስክርነት፣ሐዋ፣17፡16-34 (የቃል ጥናት፦ፍልጵ፡4፡12-13)
33. ሰላሣ ሦስተኛ ሣምንት፣ምስክርነት ሌሎችን ደቀመዝሙር ያደርጋል፣ሐዋ፣18፡18-28 (የቃል ጥናት፦ፍልጵ፡4፡12-13)
34. ሰላሣ አራተኛ ሣምንት፣ቤተሰብህን ደቀመዝሙር አድርግ፣ዘዳ፣6፡1-25 (የቃል ጥናት፦ፍልጵ፡4፡12-13)
35. <u>ሰላሣ አምስተኛ ሣምንት፣የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>
36. ሰላሣ ስድስተኛ ሣምንት፣ጳውሎስ በመጨረሻው ጉብኝት የሰጠው ማስጠንቀቂያ፣ሐዋ፣20፡17-37 (የቃል ጥናት፦ሐዋ፣20፡24)
37. ሰላሣ ሰባተኛ ሣምንት፣በድፍረት መመስከር፣ሐዋ፣22፡1-22 (የቃል ጥናት፦ሐዋ፣20፡24)
38. ሰላሣ ስምንተኛ ሣምንት፣ለምስክርነት መታዘዝ፣ሐዋ፣26፡1-29 (የቃል ጥናት፦ሐዋ፣20፡24)
39. ሰላሣ ዘጠነኛ ሣምንት፣ጳውሎስ በሮሜ የሰበከው ስብከት፣ሐዋ፣28፡16-31(የቃል ጥናት፦ሐዋ፣20፡24)
40. አርባኛ ሣምንት፣ቤተክርስቲያን ምንድናት? (የቃል ጥናት፦ሐዋ፣20፡24)

*አንደኛ ሣምንት ለክርስቶስ ምስክር መሆን ሐዋ፡1፡1-15*

*የመሪው መመሪያ፡-* በዛሬው ክፍለ ጊዜ መጨረሻ ላይ ለሌላው እንዴት ስለ ክርስቶስ እንደምትመሰክር ምሳሌ ስጥ፡፡በዚህ ጊዜ ለወንጌል ምስክርነት የሚሆን ጥቅስ መጠቀም ጥሩ ምሳሌ ይሆናል፡፡ የምትሰጠው ምስክርነት ከ5 ደቂቃ መብለጥ የለበትም፡፡ ሁሉም አባላት ምስክርነታቸውን ለማዘጋጀት በሐዋሪያ ሥራ ትምርት መጨረሻ ላይ ያለውን ክፍል እንድመለከቱ አድርግ፡፡

የቡድንህ አባላት በሚቀጥለው ሣምንት የራሳቸውን ምስክርነት እንዲያዘጋጁ ንገራቸው፡፡

*መግቢያ፡-* የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ሐዋሪያት የሠሩትን ሥራና የቤቴክርስቲያን አጀማመር ታሪክ ይናገራል፡፡ ይህ ከኢየሱስ ሥራ ወደ መንፈስ ቅዱስ ሥራ መሸጋገሪያ ነው፡፡ ከትንሣኤ በኂላ ኢየሱስ ከ40 ቀናት በፊት ለሐዋሪያት ተገለጠ፡፡ ሐዋሪያት መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አዘዛቸው፡፡ ይህ የቤቴክርስቲያን ታሪክ መጀመሪያ ነው፡፡ ታሪኩ ከሐዋ፡ 1 እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

*የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩ የበለጠ ግልጽ እንዲሆን አድርግ*

1. ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኂላ ራሱን የገለጠው ለማን ነበር?
2. እግዚአብሔር አብ ለመስጠት ቃል የገባው ስጦታ ምን ነበር?
3. ደቀመዛሙርቱ መንግሥትን በተመለከተ ኢየሱስን የጠየቁት ጥያቄ ምን ነበር? ይህ ጥያቄ ስለ መንፈሳዊ መንግሥት ነው ወይስ ስለ ምድራዊ መንግሥት? ኢየሱስ ለጥያቄአቸው ምን ምላሽ ሰጠ?
4. መንፈስ ቅዱስ በእነሱ ላይ ሲመጣ ምንን ይቀበላሉ? የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ከተቀበሉ በኂላ ምን ይሆናሉ? ለኢየሱስ ምስክር የሚሆኑት በየትኛው አገር ነው?
5. ከዚያ በኂላ ኢየሱስ ወዴት ሄደ? ቀጥሎ ማን ተናገራቸው? ሁለቱ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሰዎች ምን አሉአቸው?
6. ኢየሱስ ተለይቶአቸው ወደ ሰማይ ከሄደ በኂላ ሐዋሪያት ወዴት ሄዱ? በክፍሉ ውስጥ የነበሩት እነማን ነበሩ? ቁጥራቸው ስንት ነበር?

*የውይይት ጥያቄዎች*

1. ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
2. ምስክርነት ምንድነው?
3. ደቀመዛሙርቱ ለኢየሱስ ምስክር ያደርገናል ብለው ያዩት ወይም ያወቁት ምን ነበር? (1ቆሮ፡15፡1-8)
4. ከዚህ ታሪክ የተነሣ ለኢየሱስ ምስክር ሆነህ ሳለ በየዕለቱ በምትኖረው ኑሮ ራስህን እንዴት ታያለህ? ከሰዎች ጋር ባለህ ግንኙነት፣በመሥርያ ቤትህና በዓለም ሁሉ ለኢየሱስ ምስክር እንደሆንክ አስብ፡፡

*የቡድኑ መሪ ከ3-5 ደቂቃ ለኢየሱስ እንዴት እንደሚመሰክር ምስክርነት ይሰጣል፡፡*

*የቃል ጥናት፡- ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያ እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናለችሁ አለ፡፡(ሐዋ፡1፡8)*

*ሁለተኛ ሣምንት ለክርስቶስ ምስክር መሆን ሐዋ፡1፡1-11*

1. የባለፈውን ሣምንት ታሪክ እንደገና በቃልህ ተናገር።
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያዩ፡- ምስክርነት ምንድነው? ስለኢየሱስ ምስክርነት መስጠት ምንድነው?
3. 1ጴጥ፣3፡15 አንብብ። ለኢየሱስ ማን ምስክር መሆን አለበት? የራሳችንን ምስክርነት እንዴት መስጠት አለብን? (መልሱ፡- ረጋ ብለን መናገርና በአክብሮት መናገር።)
4. 1ቆሮ፡15፡1-8 አንብብ። ስለ ወንጌል የምንማራቸው እውነቶች ምንድናቸው?

<u>ምስክርነት መስጠት</u>

እያንዳንዱ ሰው ከ3-5 ደቂቃ የዘለቀ ምስክርነት እንዲሰጥ አድርግ። ሌሎች ደግሞ በቀጣዩ በአንድነትና በፀሎት ጊዜ ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ ንገራቸው።

ከአባላቱ ውስጥ በሚቀጥለው ጊዜ እናገራለሁ የሚሉ ካሉ እለፋቸው።
በሳምንቱ ውስጥ ወንጌልን የመመስከር ዕድል እግዚአብሔር እንዲሰጥ ፀልዩ።

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያ እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናለችሁ አለ።(ሐዋ፡1፡8)*

<u>ሦስተኛ ሣምንት ፣ የመንፈስ ቅዱስ መውረድ፣ ሐዋ፡2፡1-24</u>

<u>መግቢያ፡-</u> ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ወደ ሰማይ መሄዱን ካዩ በኋላ ወደ ላይኛው ክፍል ሄዱ። ኢየሱስ ያዘዛቸውን እያደረጉ መጠበቅ ጀመሩ። ለአሥር ቀናት ፀለዩ። ከተሰበሰበው ምርት የመጀመሪያውን ፍሬ እየበሉ የሚያከብሩበት በዓለ-ሃምሳው ቀን (ጴንጠቆስጤ) ደረሰ። ከመላው ዓለም የአይሁድ አማኞች በዓሉን ሊያከብሩት መጡ።
ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።
<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>

1. በበዓለ-ሃምሳው ቀን በደቀመዛሙርቱ ላይ ምን ወረደ?
2. ደቀመዛሙርቱ በኢየሩሳሌም በአዲስ ቋንቋ ሲናገሩ የሰሙት ማን ነበሩ?
3. ደቀመዛሙርቱ በአዳዲስ ቋንቋዎች መናገራቸውን የሰሙ አይሁድ መጀመሪያ የሰጡት ምላሽ ምን ነበር?
4. ስለተነገሩ ልሳኖች (አዲስ ቋንቋዎች) ጴጥሮስ የሰጠው ማብራሪያ ምን ነበር?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር በዚህ ታሪክ ውስጥ ሥራውን በምን ዓይነት መንገድ ይሠራል? እግዚአብሔር ይህንን ለምን የሚሠራ ይመስልሃል?
2. ከዚህ ታሪክ ስለ ኢየሱስ ምን እንማራለን?
3. እግዚአብሔር መንፈሱን በቤተክርስቲያኑ ላይ የሚያፈስሰው ለምንድነው? ቁ፣18 እና 21 እና 1ቆሮ፡14፡3 አንብብ። (**ትንቢት**፡- ወደ ፊት የሚሆነውን መናገር ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል መግለጥ የሚለውንም ያካትታል።)
4. ይህን ታሪክ ከሰማህ በኋላ ሕይወትህ እንዴት እንዲለወጥ ትፈልጋለህ?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u>ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።(ሐዋ.1፡8)*

## <u>አራተኛ ሣምንት፣ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል መዘጋጀት ሐዋ፣2:36-41</u>

ከቡድኑ አባላት ባለፈው ሣምንት ምስክርነት የሰጡ ካሉ ጠይቃቸው።

<u>*መግቢያ፦*</u> በበዓለ ሃምሳው (ጴንጠቆስጤ) ቀን መንፈስ ቅዱስ መጣ። ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር ሃይል፣ብርታትና ጥበብ ተሞላች። በብሉይ ኪዳን ዘመን መንፈስ ቅዱስ በነቢያት ወይም በካህናት ወይም በነገሥታት ላይ ይወርድ ነበር። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ አልኖረም። አንዴ ይመጣና ይሄዳል። አሁን አንድ አዲስ ነገር ይሆናል። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፦

*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*

<u>*የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።*</u>

1. ጴጥሮስ ለሕዝቡ ስለ ኢየሱስ ምን ነገራቸው?
2. ሕዝቡ ለመልክቱ ምን ምላሽ ሰጡ? እነሱ ጴጥሮስን የጠየቁት ጥያቄ ምን ነበር?
3. ጴጥሮስ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?
4. መንፈስ ቅዱስን የሚቀበለው ማን ነው?

<u>*የውይይት ጥያቄዎች*</u>

1. ከዚህ ታሪክ ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን ትማራለህ?
2. ዮሐ.7:37-39 አንብብ። ለመንፈስ ቅዱስ ስለተገባው ተስፋ ምን እንማራለን?
3. ኤፌ.1:13-14 በመንፈስ ቅዱስ ስለሚያምኑ ሰዎች ዛሬ ምን እንማራለን?
4. ራስህን በምታይበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ባንተ ይኖራል? ዳግመኛ ስለመወለድህና በመንፈስ ቅዱስ ስለመታተምህ እርግጠኛ ነህ?

*<u>የቃል ጥናት፦</u>ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።(ሐዋ.1:8)*

## <u>አምስተኛ ሣምንት ፣ የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>

ከአባላቱ አንዱ ምስክርነቱን በዛሬው የአንድነት ጊዜ እንዲናገር ማድረግ ትችላለህ። ወይም ባለፈው ሣምንት ለሌላው ምስክርነቱን የሰጠ ካለ መጠየቅ ትችላለህ።

*<u>የቃል ጥናት፦</u>ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፣በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።(ሐዋ.1:8)*

## <u>ስድስተኛ ሣምንት ፣ በቃሉ መኖር ፣ሐዋ፣2:42-47</u>

<u>*መግቢያ፦*</u> አዲስ ያመኑ ሰዎች በአዲስ ሕይወት ለመኖር ወሰኑ። ይህ አዲስ ሕይወት ሐዋሪያት እንዳስተማሩት ለእግዚአብሔር ቃል መኖርን ያካትታል። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፦

*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።

1. እነዚህ አዲስ ያመኑ ሰዎች ለመኖር የወሰኑት አራቱ የክርስቲያን ሕይወት_የሚ ያካትታቸው ነገሮች ምንድናቸው?
2. ቀጥሎ ምን ሆነ?
3. ቤተክርስቲያን ድሆችን ለመርዳት ያደረገችው ምንድነው?
4. እግዚአብሔር እንዴት ባረካቸው?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ራስን ስለመስጠት ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?
2. ለእግዚአብሔር ቃል ራስን መስጠት አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?
3. ከሚከተሉት የክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የትኛው ነው ለመኖር ያስቸገረህ፦ ፀሎት፣ሕብረት፣በቃሉ መኖር? ለምን?
4. እንደ ጥንቷ ቤተክርስቲያን ሕይወት ለመኖር በዚህ ሣምንት ውስጥ ምን ማድረግ አለብን?

*የቃል ጥናት፦ ጴጥሮስም፦ ንስሐ ግቡ፣ሃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀባላችሁ። የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው። (ሐዋ.2፡38-39)*

ሰባተኛ ሣምንት ፣የተአምራት ምስክርነት ፣ሐዋ፣3፡1-19

*መግቢያ፦* ቤተክርስቲያን በየቀኑ ታድግ ነበር። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት ይጨምር ነበር። ሕብረታቸው እውነተኛና ኢየሱስን ለመከተል የወሰነ የክርስቲያን ሕብረት ነበረ። እግዚአብሔር የሐዋሪያትን ሥልጣን ለማሳየትና ቤተክርስቲያንን ለመመሥረት በሐዋሪያት እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት አደረገ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።
ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።

የሚከተሉትን ጥያቄዎችና ሌሎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።

1. በታሪኩ መጀመሪያ ላይ ጴጥሮስና ዮሐንስ የት ነበሩ?
2. እዛ ቦታ የነበረው ማን ነበር? ጴጥሮስ ምን እንዲሰጠው ነው የጠየቀው?
3. ጴጥሮስ ምን አለ? ምንስ አደረገ?
4. ቀጥሎ ምን ሆነ?
5. ሕዝቡ የተፈወሰውን ሰው ካዩ በኋላ ምን አሉ?
6. ጴጥሮስ ቀጥሎ ምን ሆነ?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ይህንን ሰው ስለፈወሰ ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
2. ይህ ሰው እስከሚፈወስበት ቀን ድረስ እግዚአብሔር ዝም በማለቱ ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
3. ጴጥሮስ  እንዴት እግዚአብሔርን አከበረ? እግዚአብሔርን ማክበሩ ለምን አስፈለገ?
4. በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሽባ ከመሆኑ የተነሳ የፈውስና የተስፋ መልክት ያስፈልገዋል የምትለው ሰው አለ? አንተ ብትሆን እንዲህ ዓይነቱን ሰው ምን ታደርጋለህ?

*የቃል ጥናት፡- ጴጥሮስም፡- ንስሐ ግቡ፣ሃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀባላችሁ። የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው። (ሐዋ.2፡38-39)*

ስምተኛ ሣምንት ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ለኢየሱስ ቆራጥ ምስክሮች ነበሩ ፣ ሐዋ፣4፡1-31

*መግቢያ፡-* ጴጥሮስ በቤተመቅደሱ ደጅ የነበረውን ሽባ ፈወሰ። በሆነው ነገር ተደንቀው ለተሰበሰበው ሕዝብ ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ መናገር ጀመረ። ከዚያም የሃይማኖት መሪዎች መጡና ጴጥሮስና ዮሐንስን ወደ እሥር ቤት አስገቡአቸው። በሚቀጥለው ቀን ወደ ሃይማኖት መሪዎች ፊት ቀረቡ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*

*የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ*

1. የሃይማኖት መሪዎች ለምን ተቆጡ?
2. የካህናት አለቆች ጰጥሮስንና ዮሐንስን ምን ጠየቁ?
3. ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ምን ነገራቸው?
4. እንደጴጥሮስ አገላለጽ ደህንነት ሊገኝ የሚችለው ከዬት ነው?
5. ስለ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሕይወት በተመለከተ የካህናት አለቆችን የገረማቸው ምን ነበር?
6. ሽባው ሰው የተፈወሰበትን ተአምር ሸንጎው (የአይሁድ አለቆች ስብስብ) ያውቅ ነበር?
7. ጴጥሮስና ዮሐንስ ምን እንዲያደርጉ ነው ሸንጎው ያዘዘው?
8. ጴጥሮስና ዮሐንስ የሰጡት ምላሽ ምን ነበር?
9. ቀጥሎ ምን ሆነ?
10. ጴጥሮስ ስለተናገረው ሪፖርት ምዕመናን ምን አሉ?
11. ለፀሎታቸው የመጣው ምላሽ ምን ነበር?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን እንማራለን?
2. ስለ ጴጥሮስና ስለ ዮሐንስ ምን እንማራለን? ምስክርነታቸውን እንዴት ተወጡ?
3. ስለ ፀሎት ምን እንማራለን?
4. ስለ ጌታ ደፍረህ እንዳትመሰክር የራስህ ባሕል እንዴት ተጽዕኖ ያሳድርብሃል?
5. እግዚአብሔር ዛሬ ምን እንድታደርግ ይነግርሃል?

*የቃል ጥናት፡- ጴጥሮስም፡- ንስሐ ግቡ፣ሃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀባላችሁ። የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው። (ሐዋ.2፡38-39)*

ዘጠነኛ ሣምንት ፣ በታማኝነት በመኖር ምስክር መሆን ፣ሐዋ፣4፡32-5፡11

*መግቢያ፡-* የጥንቷ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ያላቸውን ሸጠው ለድሆች ያካፍሉ ነበር። የዚያን ጊዜ ሰዎች ስላላቸው ነገር የተለወጠ አስተሳሰብና ልብ ነበራቸው። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።

1. አማኞች ምን ያደርጉ ነበር? እርስ በርስ ለመረዳዳት ያደረጉት ምን ነበር?
2. ሐዋሪያት ምን ያደርጉ ነበር?
3. ባርናባስ ምን አደረገ?
4. አናንያ ምን አደረገ? ጴጥሮስ ምን አለው? ቀጥሎ ምን ሆነ?
5. ሳጵራ ምን አለች? ከዛ በኋላ ምን ሆነች?
6. ይህ በቤተክርስቲያን ላይ ምን ተጽዕኖ አመጣ?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ከዘህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን? እግዚአብሔር የሐጢአት ልምምድ በቤተክርስቲያን ሲኖር ምን ያደርጋል? ለምን?
2. ዛሬ በቤተክርስቲያን ውስጥ ገንዘባቸውን፣ጊዜአቸውንና መክሊታቸውን የሚቀብሩ ሰዎችን እግዚአብሔር ለምን አይገድልም? ይህ ሁኔታ ዛሬም እግዚአብሔርን ይገደዋልን?
3. ላንተ ያለህ ነገር ምንድነው? ዛሬ ገንዘብህን፣ጊዜህንና ስጦታህን እየቀበርክ ነህ? በዚህ ሣምንት ለውጥ የሚያስፈልግህ በየትኛው ቦታ ነው?
4. ጊዜ ካለህ ማቴ፣6፡19-21 እና ያዕቆ፣5፡3 አንብብ።

*የቃል ጥናት፡-* *ጴጥሮስም፡- ንስሐ ግቡ፣ሃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀባላችሁ። የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው። (ሐዋ.2፡38-39)*

አሥረኛ ሣምንት ፣ የአንድነትና የፀሎት ጊዜ

አሥራ አንደኛ ሣምንት ፣የአገልግሎት ምስክርነት ፣ ሐዋ፡6፡1-7

*መግቢያ፡-* እግዚአብሔር ሐዋሪያትን በመጠቀም ተአምራትንና ድንቆችን ያደርግ ነበር። ሐዋሪያት በእሥር ቤት ቢጣሉም በዚያም ስለ እግዚአብሔር ማስተማርና መስበክ ቀጠሉ። ስለ ኢየሱስ መከራ ቢቀበሉም ደስተኞች ነበሩ። የሚድኑ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ ችግሮች መፈጠር ጀመሩ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ

1. ሲያጉረመርሙ የነበሩት እነማን ነበሩ? ለምን?
2. 12ቱ ቀድመው ያደረጉት ምን ነበር 12ቱ ለማድረግ የወሰኑት ምን ነበር?
3. ምግቡን እንዲያስተናግድ የተመረጠው ማን ነበር? 7ቱን ሰዎች የመረጠው ማን ነበር? የተመረጡበት መመዘኛዎች ምን ነበሩ?
4. ለዚህ ውጤቱ ምን ነበር?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ከዚህ ታሪክ ስለጥንቷ ቤተክርስቲያን ምን እንማራለን?
2. ስለ አገልግሎት ምን እንማራለን? የምንወዳቸውን ሰዎች ብቻ ነው የምናገለግለው?
3. አንድን ሰው እንድትረዳ የተጠየቅኽበትን ጊዜ አስብ። ያንን ሰው የረዳኸው ደስ ብሎህ ነው ወይስ መርዳቱ ግድ ስለሆነብህ ነው? ቆላ፣3:17 አንብብና ከቡድኑ ጋር ተወያዩ።
4. የቤተክርስቲያን መሪዎች ለእግዚአብሔር ቃልና ለፀሎት ጊዜ እንዲኖራቸው እንዴት መርዳት እንችላለን?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሁሉ ሥራ እንድ እንዳይደለ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። (ሮሜ፡12፡4-5)*

*<u>አሥራ ሁለተኛ ሣምንት ፣ የአገልግሎት ምስክርነት</u>*

*<u>የውይይት ጥያቄ፡</u>*-በየቡድናችን አንድን ሰው ለማገልገል ማድረግ የምንችላቸውን ነገሮች ምንድናቸው? ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖረን እንፀልይ፣ ደግሞም በሚቀጥለው ሣምንት አንድን ሰው ማገልገል የምንችልባቸውን ሥራዎች እናቅድ። ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ነገሮች በዕቅድህ ማካተት ትችላለህ፡-

1. ለታመመ ወይም ገንዘብ ለሌለው ሰው ምግብ መውሰድ።
2. የጎረቤትህን ደጅ ወይም ቤት በመጥረግ ማገዝ።
3. ጎረቤትህ ዘር ሲዘራ ማገዝ።
4. በመንገድ ላይ ወይም በቤተክርስቲያንህ አካባቢ ያለውን ቆሻሻ ማንሳት።
5. ከቤተክርስቲያንህ መጋቢ ጋር ታማሚዎችን መጎብኘት።

ኤፌ፣6፡5-8 አንብብና ተወያዩ።

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሁሉ ሥራ እንድ እንዳይደለ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። (ሮሜ፡12፡4-5)*

*<u>አሥራ ሦስተኛ ሣምንት ፣ መስዋዕት በመሆን መመስከር ፣ሐዋ፣7</u>*

*<u>የመሪው መመሪያ፡-</u>* ይህንን ታሪክ ለየት ባለ መልኩ መናገር የምትችልበትን መንገድ ለመፍጠር ሞክር። እስጢፋኖስ የተናገረውን ንግግር አጠር አድርገህ መናገር ትችላለህ ካልሆነ ደግሞ ንግግሩን ከፋፍለህ ከቡድንህ አባለት ሶስት ወይም አራት ሰዎች እንዲናገሩ ማድረግ ትችላለህ።
*<u>መግቢያ፡-</u>* እስጢፋኖስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን መበለቶች ለማገልገል ከተመረጡ ዲያቆናት አንዱ ነበር። አይሁዶች በሐሰት ከሰሱት። በሸንጎው (አይሁድ ገዢዎች ቡድን) ፊት ቆመ። በእግዚአብሔር፣በሙሴና በቤተመቅደስ ላይ እነሱ እንደሚያስቡት የነቀፋ ቃላቶችን በመናገሩ ተከሰሰ። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-
*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*
*<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>*

1. እስጢፋኖስ ለሊቀ ካህናቱ እንዴት መለሰለት? እሱ የነገረላቸው የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች እነማን ነበሩ?
2. ስለ መገናኛ ድንኳን ምን ነገራቸው?

3. በቁ፣51 ላይ እስጢፋኖስ በሸንጎው ውስጥ የነበሩ ሰዎችን ምን ብሎ ጠራቸው?
4. በኋላ እስጢፋኖስ ምን ሆነ?
5. እርሱ በሞት ጣር እያለ ምን አለ?
6. እስጢፋኖስ እንዲሞት በዚያ ሥፍራ የተስማማው ማን ነበር?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር ሕዝቡ ሲሰደዱና ሲገደሉ ለምን ዝም ይላል? ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ዘላለማዊ ዕቅዱ ምን እንማራለን?
2. እስጢፋኖስ ለምን ተገደለ? እውነተኛ ምክንያት ምን ነበር?
3. ለእምነትህ ስትል ዛሬ ስደት በአንተ ላይ በምን መልኩ ነው የሚመጣው?
4. ከእስጢፋኖስ ሕይወት ምን እንማራለን?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሁሉ ሥራ እንድ እንዳይደለ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። (ሮሜ፡12፡4-5)*

*<u>አሥራ አራተኛ ሣምንት ፣ የመስካሪ ግዴታ ፣ሐዋ፣8፡26-40</u>*

*<u>መግቢያ፡-</u>* ባለፈው ሣምንት የእስጢፋኖስ መገደል ተምረን ነበር። ሌላው ከ7ቱ ዲያቆናት አንዱ ፊልጶስ ነበር። እርሱም ታማኝ የእግዚአብሔር ሰው ነበር። ታሪኩ ከሐዋ፣8 እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>

1. ፊልጶስ ወደ መንገዱ እንዲሄድ የነገረው ማን ነበር?
2. ፊልጶስ ሲሄድ ማንን አገኘ? ይህ ሰው ምን ያደርግ ነበር?
3. ፊልጶስ ቀጥሎ ምን አደረገ? ቀጥሎ ምን አለ?
4. ቀጥሎ ምን ሆነ? ፊልጶስ ቀጥሎ ወዴት ሄደ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር በኢትዮጵያዊው ሕይወት እንዴት ይሠራ ነበር? በፊልጶስ ሕይወትስ?
2. ለእግዚአብሔር ምሪት ፊልጶስ ምን ምላሽ ሰጠ?
3. ኢትዮጵያዊው ለእግዚአብሔርና ለፊልጶስ ምን ምላሽ ሰጠ?
4. ሌሎችን ደቀመዝሙር ለምታደርገው ሥራ ድርሻህን እንድታውቅ ይህ ታሪክ እንዴት ይረዳሃል?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሁሉ ሥራ እንድ እንዳይደለ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። (ሮሜ፡12፡4-5)*

***<u>አሥራ አምስተኛ ሣምንት ፣ የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>***

ከሶዶ ክርስቲያን ሆስፒታል ራዕይ አንዱ ወንጌልን ላልሰሙ መመስከርና ደቀመዛሙርትን ማፍራት ነው። በዛሬው የአንድነት ጊዜ ለዚህ ራዕይ ፀልዩ። በሁለተኛ ሣምንት እንዳደረግነው ይህ ጊዜ ምስክርነትን ለመስጠት ምቹ ጊዜ ነውና መለማመድ ትችላላችሁ።

*<u>አሥራ ስድስተኛ ሣምንት ፣የመታዘዝ ምስክርነት ፣ሐዋ፣</u>*<u>9:1-19</u>

*መግቢያ፡- የፊልጶስንና የኢትዮጵያዊውን ታሪክ አጥንተን ነበር። በዚያን ጊዜ የጌታ መልዓክ ወደ ፊልጶስ መጥቶ ወደ ደቡብ በኩል እንዲሄድ ነገረው። በዚህ ጊዜ ፊልጶስ ለመልዕክቱ ታዝዞ ሄደና ለኢትዮጵያዊው ወንጌልን መሰከረ። ኢትዮጵያዊው መልዕክቱን ወደ ቤት ይዞ ሄደ። ሌሎች አህዛብ ወንጌልን እንዲሰሙ እግዚአብሔር ስላቀደው ዕቅድ አሁን እንማራለን። ዕቅዱ ቤተክርስቲያንን በሚያሳድደው ሳውል ይጀምራል። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-*

*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*

*<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>*

1. *ሐዋሪያው ጳውሎስ ለምን ወደ ደማስቆ ለመሄድ  ፈለገ?*
2. *በጉዞ ላይ ምን ሆነ?*
3. *ኢየሱስ ለጳውሎስ ምን ነገረው?*
4. *እግዚአብሔር ለሐናንያ ምን ነገረው?*
5. *ቀጥሎ በጳውሎስ ላይ ምን ሆነ?*

*<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>*

1. *ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን? ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን እንማራለን?*
2. *ስለ መታዘዝ ምን እንማራለን?*
3. *በዚህ ታሪክ ካሉ ሰዎች ውስጥ የትኛውን ትመስላለህ፡- ጳውሎስን ወይስ ሐናንያን? ለምን?*
4. *ከዚህ ታሪክ ስለ ፍርሃትና በእግዚአብሔር ላይ እምነትን ስለ መጣል ምን እንማራለን?*

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ይህን በሰሙ ጊዜም ዝም አሉና፡- እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ። ሐዋ፣11:18*

*<u>አሥራ ሰባተኛ ሣምንት ፣የተለወጠ ሕይወት ምስክርነት ፣ሐዋ፣</u>*<u>9:20-31</u>

*<u>መግቢያ፡-</u> ባለፈው ሣምንት ስለ ሳውልና በደማስቆ መንገድ ላይ ሳለ ጌታ እንዴት ሕይወቱን እንደለወጠ ተምረን ነበር። ሐናንያ ለእግዚአብሔር እንደታዘዘና እግዚአብሔር ላሳውል ባቀደው የሕይወት ለውጥ ዕቅድ ውስጥ የራሱን ድርሻ እንዳበረከተ አይተን ነበር። በዚህ ሣምንት ቤተክርስቲያን ለሐዋሪያው ጳውሎስ ምን ምላሽ እንደሰጠች እንመለከታለን። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-*

*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*

*<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>*

1. *በአንድ ጊዜ ጳውሎስ ሊያደርግ የጀመረው ምን ነበር?*
2. *ሕዝቡ ምን ምላሽ ሰጡ?*
3. *ጳውሎስን ለመግደል የፈለገው ማን ነበር? ከዚያ በኂላ ምን ሆነ?*
4. *በኢየሩሳሌም ምን ሆነ? ጳውሎስን የረዳው ማን ነበር?*

*<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>*

1. ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔርና እርሱ ስለሚጠቀመው ሰው ምን እንማራለን?
2. እግዚአብሔር ጳውሎስን ለወጠው። ሕይወትህ ከኢየሱስ የተነሣ መለወጡን ሌሎች በቀላሉ ማየት ይችላሉ?
3. ቀድሞ በጣም ሐጢአተኛ ለነበሩ አዲስ አማኞች እንዴት ምላሽ ትሰጣለህ?
4. በሕይወትህና በቤተክርስቲያንህ ለውጥ የሚያስፈልገው ምንድነው?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ይህን በሰሙ ጊዜም ዝም አሉና፡- እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ። ሐዋ፣11፡18*

<u>*አሥራ ስምንተኛ ሣምንት* ፣ጥላቻን የማሸነፍ ምስክርነት ሐዋ፣10፡1-29፣34-35</u>

*<u>መግቢያ፡-</u>* ሐዋሪያው ጴጥሮስ የታመሙትን እየፈወሰና ወንጌልን እየሰበከ በእዮጴና በልዳ ይጓዝ ነበር። የሞተውን ሰው አስነሳ። ከዚያም ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ለማመን መጡ። በዚህ ሳምንት እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያቀደውን ዕቅድ እንማራለን።

ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ታሪኩን ተናገር፣ተናገር።

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።

1. በኢየሩሳሌም ያሉ አማኞች ለምን ጴጥሮስን ተቹት?
2. ጴጥሮስ በራዕይ ምን አየ?
3. ወደ ጴጥሮስ የመጣው ማን ነበር? ጴጥሮስ ምን እንዲያደርግ ነው መንፈስ ቅዱስ የነገረው?
4. ቆርኔሌዎስ በጴጥሮስ እግር ላይ ሲወድቅ ጴጥሮስ ምን አለው?
5. ጴጥሮስ የጣሰው የአይሁድ ሕግ ምን ነበር?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ምን እንማራለን?
2. ስለ ጥንቷ ቤተክርስቲያን ምን እንማራለን?
3. ጴጥሮስ የአይሁድን ሕግ ጥሶ ወደ አሕዛብ ቤት የገባው ለምንድነው?
4. ሰው ያገለለኛል ብለህ የምትፈራው ነገር ምን አለ?
5. እግዚአብሔር እንዲጠቀምብህ ይህንን ፍርሃት እንዴት ልታስወግድ ትችላለህ?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ይህን በሰሙ ጊዜም ዝም አሉና፡- እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ። ሐዋ፣11፡18*

<u>*አሥራ ዘጠነኛ ሣምንት* ፣የቤተክርስቲያን አገልግሎት ፣2ቆሮ፡5፡14-21</u>

*<u>መግቢያ፡-</u>* ሐዋሪያው ጳውሎስ በግሪክ ሀገር ቆሮንቶስ ከተማ ላሉ ምዕመናን ይጽፋል። ስለተሰጣቸው አገልግሎት ያሳስባቸዋል።

ታሪኩን ተናገር ፣ታሪኩን ተናገር።

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔርና ከእርሱ ጋር ግንኙነት እንድናደርግ ለእኛ ስለሰጠው ዕድል ምን እንማራለን?
2. በቁ፣7 ላይ እግዚአብሔር አንተንና ሌሎችን እንዴት እንደሚያይ ምን ትማራለህ?
3. የእርቅ መልክተኛ ማለት ምን ማለት ነው?
4. እኛ ለማን መኖር አለብን?
5. ይህ ክፍል እንዴት ለውጥ እንድታመጣ ያነሳሳሃል?

*<u>የቃል ጥናት</u>፡- ይህን በሰሙ ጊዜም ዝም አሉና፡- እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ። ሐዋ፤11፡18*

<u>ሃያኛ ሣምንት ፤የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>

<u>ሃያ አንደኛ ሣምንት ፤ጴጥሮስ ከእሥር ቤት ወጣ ፤ሐዋ:12:1-19</u>

<u>መግቢያ፡-</u> በኢየሩሳሌም የነበሩ ምዕመናን ጌታን ስለተቀበሉ ሰዎች ማለትም ስለ ቆርኔሌዎስና ስለ ሌሎች አሕዛብ ጴጥሮስን ጠየቁት። መሪዎቹ ተወያይተው፡- ‹‹አሕዛብን ይቅር ያለና ወደ ሕይወት የመራቸው እግዚአብሔር ነው›› ለማለት ወሰኑ። ቤተክርስቲያን እያደገች ስለ ሄደች ንጉሡ ሄሮድስ ቤተክርስቲያንን ማሳደድ ጀመረ።

ታሪኩን ተናገር።

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>

1. በሰይፍ የተገደለው ማን ነበር?
2. ንጉሡ ቀጥሎ የያዘው ማን ነበር?
3. ይፀልይ የነበረው ማን ነበር?
4. በምሽት ምን ሆነ?
5. መልዓኩ ጴጥሮስን ምን አለው?
6. ቀጥሎ ምን ሆነ?
7. ጴጥሮስ ነፃ ስለመውጣቱ ሄሮድስ ምን ምላሽ ሰጠ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ከዚህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ባሕሪው ምን እንማራለን?
2. ሕይወትህ በወጥመድ ውስጥ ቢገባ ነፃ ለመውጣት ምን ታደርጋለህ? በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆን ነፃ መውጣት ትችላለህ?
3. ስለ ፀሎትና ከፍርሃት፤ከሁኔታዎች፤ከዓለምና ከመሳሰሉት ነፃ ስለመውጣት ምን እንማራለን?
4. ከዚህ ታሪክ የተነሣ በሕይወትህ ምን ዓይነት ለውጥ እንዲመጣ ትፈልጋለህ

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤ ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፤ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።(ኤፌ፡4፡15-16)*

<u>ሃያ ሁለተኛ ሣምንት ፤ለጌታ የተሰጠ ሕይወት ፤ሐዋ፤12፡25-13፡5</u>

<u>መግቢያ፡-</u> ሄሮድስ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ስላልሰጠ እግዚአብሔር ቀሰፈው። የምሥራቹ ወንጌል በዓለም ሁሉ መሰበኩን ቀጠለ። ታሪኩ ከሐዋ፤12 እንደሚከተለው ቀርቧል። ታሪኩን ተናገር፤ታሪኩን አንብብ።

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>

1. ወደ አንጾኪያ የተመለሰው ማን ነበር?
2. ይፆምና ይፀልይ የነበረው ማን ነበር?
3. መንፈስ ቅዱስ ምን ነገራቸው?
4. ቀጥሎ ምን ሆነ?

5. ከዚያ በኂላ የት ሄዱ? ምንስ አደረጉ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ሰዎች ሲፀልዩና ሲያመልኩ ለምን እግዚአብሔር ምሪትን ሰጣቸው?
2. ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት በእግዚአብሔር ፊት መጾም ምን አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል?
3. መጾም የምንችልባቸውን መንገዶችንና ጾም ሊያመጣ የሚችለውን ጥቅም ተወያዩ። መቀደስ ማለት ለአንድ የተለየ ዓላማ መለየት ማለት ነው።
4. አንተ ለእግዚአብሔር ማንን ወይም ምንን እንድትቀድስለት ነው እግዚአብሔር የሚፈልገው?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፣ ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፣ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።(ኤፌ፡4፡15-16)*

<u>*ሃያ ሦስተኛ ሣምንት ፣የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ፣ሐዋ፣*12፡25-13፡5</u>

*<u>መግቢያ፡-</u>* ቤተክርስቲያን ምሪት አስፈለጋት። ይህ በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልነበረም። እነርሱ ወንጌልን ለዓለም እንዲያደርሱ እግዚአብሔር እንደነገራቸው ያውቁ ነበር። ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወቅ ፈለጉ። መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ በቃሉ በኩል እግዚአብሔርን እንሰማዋለን፣ከመጽሐፍ ቅዱስም እውነት ውጭ አንወጣም፣ወይም እንደፈለግን አንተረጉመውም።

*ታሪኩን እንደገና ተናገር፣ አሁን አንብበው።።*

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት እንዲረዳት ምን ታደርግ ነበር?
2. የእግዚአብሔርን ድምጽ በትክክል መስማት እንድንችል የሚረዱን ሕጎች ምንድናቸው?
3. የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማትህን በምን ታውቃለህ?
4. እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል ይናገራል። ድምጹን መስማት ከፈለግህ ቃሉን ማንበብ አለብህ። እግዚአብሔር በዕቅዱ አንተን የመራበትን ጊዜ ተናገር።
5. የእግዚአብሔር ድምጽ መስሎህ በራስህ ሃሳብ የተወሰድክበት ጊዜ አለ? በመጨረሻ የሚሆነውን ነገር በምን አወቅህ?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፣ ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፣ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።(ኤፌ፡4፡15-16)*

<u>*ሃያ አራተኛ ሣምንት ፣*አጥቢያ ቤተክርስቲያን ምስክርነት</u>

*<u>መግቢያ፡-</u>* ሐዋሪያው ጳውሎስ በመጀመሪያው የወንጌል ሥርጭት ጉዞው በእስያ ክፍለ ሀገራት ቤተክርስቲያናትን አቋቋመ። ከዚያም በኂላ ቤተክርቲያናት ምዕመናንን እንድንከባከቡአቸው የማበረታቻ ደብዳቤ ጻፈላቸው። ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን የተጻፈው ደብዳቤ ቀጥሎ ቀርቧል። በአካል ውስጥ እንዳሉ የተለያዩ ክፍሎች ቤተክርስቲያንን ለማመሳሰል ሞክር። ከዚያም አንድ ላይ አንብቡ።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ከዚህ ታሪክ ስለ ቤተክርስቲያን ምን እንማራለን? ለምንድነው እግዚአብሔር አንድ አካል ውስጥ እንድንሆን የፈለገው?
2. በቤተክርስቲያን ውስጥ ስላለው እያንዳንዱ አባል ምን እንማራለን?
3. ቤተክርስቲያንህን መከታተል ለምን ይጠቅማል?
4. ይህንን ቃል ለመታዘዝ ምን ማድረግ አለብህ?

የቃል ጥናት፡- *ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፣ ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፣ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።(ኤፌ፡4፡15-16)*

*ሃያ አምስተኛ ሣምንት ፣ የፀሎትና የአንድነት ጊዜ*

*ሃያ ስድስተኛ ሣምንት፣የሚስዮናዊያን (የወንጌል መልክተኞች) ምስክርነት* ፣ሐዋ፡14፡1-7

*መግቢያ፡-* ሐዋሪያው ጳውሎስና ባርናባስ የመጀመሪያውን የወንጌል ስርጭት ጉዞአቸውን ቀጠሉ። በሄዱበት ሁሉ ኢየሱስን ይመሰክሩ ነበር። በአንድ ከተማ የሆነው ነገር ቀጥሎ ቀርቧል፡-

*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*

*የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።*

1. በሄዱበት ከተማ ሁሉ ጳውሎስና ባርናባስ በመጀመሪያ የት ይገቡ ነበር? ለምን?
2. ከዚያስ ምን ሆነ?
3. ያላመኑ አይሁድ ያስነሱት ሤራ ምን ነበር?
4. ጳውሎስና ባርናባስ ቀጥሎ ምን አደረጉ?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ወንጌልን ስንመሰክር ስለ እኛ ድርሻ፣ስለ እግዚአብሔር ድርሻና ስለምንሰክርላቸው ሰዎች ድርሻ ምን እንማራለን?
2. በቁ፣3 መሠረት በዚህ ታሪክ ውስጥ ተአምራት የመደረጋቸው ዓላማ ምን ነበር?
3. ተአምራት ሁል ጊዜ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ሰዎችን ሊያሳምኑ ይችላሉን?
4. ወንጌልን ስንመሰክር መከተል ያለብን የጳውሎስ ምሳሌ ምንድነው?

*የቃል ጥናት፡- ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። (ሮሜ፡12፡18)*

*ሃያ ሰባተኛ ሣምንት* ፣አርነት ፣ሐዋ፡15፡1-29

*ለመሪው፡-* በአይሁድ ሕግ ምክንያት የሚነሣው ጥላቻ ችግር እየፈጠረ ነበር። ምናልባት የቡድንህ አባላት የሚፈልጉት ሕጉን ማጥናት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ጠቃሚ የሚሆነው በቤተክርስቲያን ውስጥ ጥላቻ የሚወገድበትን መንገድ ማጥናት ነው። ቤተክርስቲያን ሰላምን ለማምጣት እንዴት አብረው እንደሠሩ በማጥናት የበለጠ ጊዜ እንዲወስዱ ማድረግ አለብህ።

*መግቢያ፡-* ሐዋሪያው ጳውሎስና ባርናስ ወደ አንጾኪያ ተመልሰው የሆነውን ሁሉ እና እግዚአብሔር የአሕዛብን ልብ ለወንጌል መክፈቱን ተናገሩ። ቢሆንም ግን የአይሁድ ሕግ የሚጠይቀውን መስፈርት ባለማሟላታቸው ምክንያት ግጭት ይፈጠር ነበር። ቀጥሎ የሆነው ከዚህ በታች ቀርቧል።

*ታሪኩን ተናገር፣ ታሪኩን አንብብ።*

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>

1. ከይሁዳ አገር የመጡ ሰዎች በአንጾኪያ የነበሩትን ምዕመናን ያስተምሩ የነበሩት ምን ነበር?
2. ሐዋሪያው ጳውሎስ ለዚህ ምን ምላሽ ሰጠ?
3. በኋላ ምን ለማድረግ ወሰኑ? ወዴት ሄዱ?
4. ስለተፈጠረው አለመስማማት ሐዋሪያትና የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ምን አደረጉ?
5. የጴጥሮስ ምላሽ ምን ነበር?
6. ያዕቆብ ምን አለ?
7. ቤተክርስቲያን በአጠቃላይ ምን ለማድረግ ወሰነች?
8. ለአህዛብ አማኞች ምን የሚል መልዕክት ላኩ? ማነው የሄደው?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ሰዎች የሚድኑት እንዴት ነው? ይህንን ታሪክ በመጠቀም ምላሽ ስጥ::
2. ቤተክርስቲያን ጥላቻን ለማስወገድ አንድ ላይ ከሠራችው ሥራ ምን እንማራለን?
3. ለሌሎች መሰናከያ ላለመሆን ሐዋሪያው ጳውሎስ ለአይሁድ ሕግ ታዘዘ። በክርስቶስ ነጻነት ስላለህ ሌሎች በአንተ እንዲሰናከሉ የምታደርገው ነገር አለ?
4. ለሌሎች ስትል መተው ያለብህ ነገሮች ምንድናቸው?

*<u>የቃል ጥናት፦</u> ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። (ሮሜ፡12፡18)*

<u>*ሃያ ስምንተኛ ሣምንት* ፣ በመስካሪዎች መካከል የተነሳው ክርክር ፣ ሐዋ፣15:36-16:5</u>

*<u>መግቢያ፦</u>* ሐዋሪያው ጳውሎስና ባርናባስ የኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪዎች የፃፉትን ደብዳቤ ይዘው ወደ አንፆኪያ ተመለሱ። በአንጾኪያ ያሉ ምዕመናን በሙሉ በረቱ፣ጠነከሩም። ቃሉን መስበክ ቀጠሉ። ከዚያም ሁለተኛ የሚስዮናዊ (የወንጌል መልክተኛ) ጉዞ ለማድረግ ወሰኑ። *ታሪኩ ቀጥሎ ቀርቧል፦*

*ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።*

<u>የሚከተሉትና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>

1. ሐዋሪያው ጳውሎስ ወዴት ለመሄድ ፈለገ? ለምን?
2. ባርናስ ከራሳቸው ጋር ለመውሰድ የፈለገው ማን ነበር? ጳውሎስ በሃሳቡ ያልተስማማው ለምንድነው?
3. ቀጥሎ ምን ሆነ?
4. ጳውሎስ ወዴት ሄደ? ማንን አገኘ?
5. ቀጥሎ ምን ሆነ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ከዚህ ታሪክ ስለ ጳውሎስና ባርናባስ ምን እንማራለን? ስለማርቆስ ምን ዓይነት አቋም ያዙ? ለምን?
2. አንተስ ከእነዚህ (ማርቆስ ከተባለው ዮሐንስ፣ጳውሎስ ወይም ባርናባስ ከተባሉ) ሰዎች የትኛውን ትመስላለህ? ለምን?
3. ምንም እንኳ ይህ ክርክር በመካከላቸው ቢነሳም እግዚአብሔር የሠራው መልካም ነገር ምንድነው?
4. በክርስቲያኖች መካከል አንዳንድ ጊዜ አለመስማማት ይኖራል። በሌሎች አማኞች መካከል የሚነሳውን ክርክር ስለማስወገድ ምን እንማራለን?

*<u>የቃል ጥናት፦</u> ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። (ሮሜ፡12፡18)*

## ሃያ ዘጠነኛ ሣምንት ፣ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ፣1ጢሞ፣3:1-15

*መግቢያ፡-* ሐዋሪያው ጳውሎስና ባርናባስ በሁሉም ቤተክርስቲያናት ሽማግሌዎችን ሾሙ። ሐዋሪያው ጳውሎስ የቤተክርስቲያን መሪዎችን እንዲያስተምር ለጢሞቴዎስ መልዕክት ፃፈለት። ሽማግሌ የሚለው ቃል መጋቢ፣የቤተክርስቲያን መሪ፣ ወይም የአንድ ስብሰባ መሪ የሚለውን ሊወክል ይችላል። ሰዎች ታዋቂና ሃይለኛ ስለሆኑ የቤተክረስቲያን መሪ ተደርገው መመረጥ የለባቸውም። ወደ ትልቅ ሃላፍነት የሚወጡ ሰዎች ስለሆኑ በጥንቃቄ መመረጥ አለባቸው። ክፍሉን ሁለት ጊዜ ደጋግማችሁ አንብቡ።

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።

1. ለኤጲስ ቆጶስነት (ቤተክርስቲያንን ለመምራት) ፣ለዲያቆንነት ወይም ሴቶችን ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚያበቁ መመዘኛዎችን ዘርዝር።
2. አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያን ሠራተኞች ሥራቸው በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ለቤተሰቤ በቂ ጊዜ ባይኖረኝ ግድ የለም ብለው ያስባሉ። ስለዚህ ነገር ቁ፣3 እና 4 ምን ያስተምሩናል?
3. በቁ፣15 ላይ ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን እንዴት ይገልፃታል?
4. አሁን በመሪነት ሥልጣን ላይ አለህ ወይስ የመሪነት ሥልጣን ትፈልጋለህ? ራስህን የላቀ ሥራ በሚሠራው ጳውሎስ ቦታ አስቀምጠህ መዝን። በእግዚአብሔር መንገድ ለመኖር በዚህ ሳምንት ምን ማድረግ አለብህ?

*የቃል ጥናት፡- ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ። (ሮሜ፡12፡18)*

## ሰላሣኛ ሣምንት ፣ የአንድነትና የፀሎት ጊዜ

## ሰላሣ አንደኛ ሣምንት ፣ የመከራ ጊዜ ፣ ሐዋ፡16፡16-34

*መግቢያ፡-* ሐዋሪያው ጳውሎስ ከመስካሪ ቡድኑ ጋር ወደ ፊልጵስዩስ ሄዱ። በስብከታቸው ልድያ የተባለች ሴት ጌታን ተቀበለች። በዚያ ሥፍራ የሆነው ነገር ቀጥሎ ቀርቧል።
ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።

1. ጳውሎስን ስትከተል ስለነበረችው ገረድ ተናገር።
2. ጳውሎስ ይህችን ሴት ምን አደረጋት?
3. የገረዲቱ ጌቶች ምን አደረጉ?
4. ጳውሎስንና ስላስን ምን አደረጓቸው?
5. ጳውሎስና ስላስ በወኅኒ ምን አደረጉ?
6. ቀጥሎ ምን ሆነ?
7. የወኅኒ ጠባቂው ምን አደረገ?

የወይይት ጥያቄዎች

1. አንተ ብትገረፍና ወደ ወኅኒ ብትጣል ምን ታደርግ ነበር?
2. ጳውሎስና ስላስ ምን አደረጉ? ውጤቱስ ምን ነበር?
3. በሕይወትህ ያለአግባብ የሚደርስብህን ነገር እንዴት ትወጣዋለህ?
4. በሚቀጥለው ጊዜ ችግር ቢደርስብህ እንዴት ትሆናለህ?

*የቃል ጥናት፡- መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፣ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ። ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ። (ፊልጵ፡4፡12-13)*

ሰላሣ ሁለተኛ ሣምንት ፣የእውነት ምስክርነት ፣ ሐዋ፣17፡16-34

መግቢያ፡- ጳውሎስና ስላስ የወንጌል ስርጭት ጉዞአቸውን ቀጠሉ። በተሰሎንቄና በቤርያ ከተሞች ሰበኩ። የቤርያ ሰዎች የጳውሎስን ትምህርት እውነት ይሁን ውሸት ለመስማት ፈቃደኛ ስለነበሩ ልበ ሰፊዎች ተባሉ። ከዚያም ጳውሎስ ወደ አቴና አቀና። ቀጥሎ የሆነው ነገር ከዚህ በታች ቀርቧል፡-

*ታሪኩን ተናገር።*

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ *ታሪኩን* የበለጠ ግልጽ አድርግ።

1. የጳውሎስን *መንፈስ* በአቴና ያበሳጨው ምን ነበር?
2. ከዚህ የተነሣ ምን አደረገ?
3. ሕዝቡ ምን ምላሽ ሰጡ?
4. በቁ፣22 እና 23 ላይ ጳውሎስ እንዴት የአቴናን ሰዎች አምልኮ ገለፀ?
5. ጳውሎስ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ኢየሱስ ምን አለ?
6. ውጤቱስ ምን ነበር?

የውይይት ጥያቄዎች

1. የግሪክ ሰዎች በሚገባቸው መንገድ ጳውሎስ መልዕክቱን ተናገረ። ለሙስልሞችና ለሌሎች ሰዎች ወንጌልን ለመመስከር እንዴት በተሻለ መንገድ ራሳችንን ማዘጋጀት እንችላለን?
2. ሌሎች እግዚአብሔርንና ኢየሱስን የበለጠ እንዲያውቁ እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን?
3. ምንም እንኳ ለግሪክ ሰዎች የማይመች ቢሆንም ጳውሎስ በመልዕክቱ ፍርድ እንዳለ ተናገረ። ለመናገር ካሰብከው መልዕክት ወደ ኋላ አስቀርተህ ታውቃለህ?
4. ወንጌልን ለመመስከር ብቁ ለመሆን ምን ማድረግ አለብህ?

*የቃል ጥናት፡- መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፣ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ። ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ። (ፊልጵ፡4፡12-13)*

ሰላሣ ሦስተኛ ሣምንት ፣ምስክርነት ሌሎችን ደቀመዝሙር ያደርጋል፣ሐዋ፣18፡18-28

መግቢያ፡- ጳውሎስ አቂላንና ጵርስቅላን በቆሮንቶስ ከተማ አገኛቸው። ከእነርሱ ጋር ድንኳን ይሰፋና በየሰንበቱም ይሰብክ ነበር። ቀጥሎ የሆነው ከዚህ በታች ቀርቧል፡-

*ታሪኩን ተናገር።*

የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ *ታሪኩን* የበለጠ ግልጽ አድርግ።

1. ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ከተማ ወጥቶ ወዴት ሄደ? ከእሱ ጋር የሄደው ማን ነበር?
2. ቀጥሎ ጳውሎስ ወዴት ሄደ በዚያ ምን ያደርግ ነበር?
3. አቂላና ጵርስቅላ ለአጵሎስ ምን አሉ?
4. ውጤቱ ምን ሆነ?

የውይይት ጥያቄዎች

1. ከጳውሎስ ምሳሌ ምን እንማራለን?
2. ጳውሎስ የሠራው የወንጌል ምስክርነት ሥራ ተባዝቶ ከአቂላ ወደ አጵሎስ እንደተሸጋገረ እናያለን። እኛስ ለዚህ ዓይነት ሂደት ተጠርተናል ወይ? ለምን?

3. በዚህ ሂደት ውስጥ በየትኛው ቦታ ነው ራስህን የምታስቀምጠው?
4. በዚህ ሂደት ውስጥ ራስህን የበለጠ ለማስቀመጥ ምን ለውጥ ማድረግ አለብህ?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፣ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ። ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ። (ፊልጵ፡4፡12-13)*

<u>ሰላሣ አራተኛ ሣምንት ፣ቤተሰብህን ደቀመዝሙር አድርግ ፣ዘዳ፣6፡1-25</u>

*<u>መግቢያ፡-</u>* ባለፈው ሣምንት ደቀመዛሙርት መሆንና ደቀመዝሙርን የሚያፈሩ ሰዎች ስለሚለው የእግዚአብሔር ዕቅድ ተወያይተን ነበር። በዚህ ሣምንት ለቤተሰቦቻችን ስላለን ሃላፊነት እንወያያለን።

ዘዳ፣6፡1-25 አንብብ።

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ዘርዝር።
2. እነዚህን ትዕዛዛት እንድናከብር እግዚአብሔር ለምን ይፈልጋል?
3. እነዚህን ትዕዛዛት በእጅህ ምልክት አድርገህ እሰረው፣በዓይኖችህም መካከል እንደክታብ ይሁንልህ፣በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ዘመን ይህ ምን ማለት ነው? ላንተስ በግልህ ምን ይህ ትርጉም ይሰጣል?
4. ለሚቀጥለው ትውልድ ምን እንድናደርግ ነው እግዚአብሔር የሚያዝዘን?
5. መቼና የት ነው ስለ እግዚአብሔር ትዕዛዛት የምናወራው? ለአባትና ለእናት ይህ ምን ማለት ነው?
6. ልጆችህ በጌታ ያለህን እምነት በአንተ ውስጥ ያያሉ? ጥያቄስ ይጠይቃሉ? የአንተ ሃላፊነት ምንድነው?
7. የእግዚአብሔርን እውነት ለቤተሰብህ ለማስተላለፍ ምን ታደርጋለህ?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፣ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ። ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ። (ፊልጵ፡4፡12-13)*

<u>ሰላሣ አምስተኛ ሣምንት፣ የአንድነትና የፀሎት ጊዜ</u>

<u>ሰላሣ ስድስተኛ ሣምንት ፣ ጳውሎስ በመጨረሻው ጉብኝት የሰጠው ማስጠንቀቂያ ፣ሐዋ፣20፡17-37</u>

*<u>መግቢያ፡-</u>* ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ ነው። የኤፌሶን ቤተክርስቲያን መሪዎችን ዳግመኛ እንደማያገኛቸው ያውቃል። የጳውሎስ መጨረሻ ትምህርቱና ማስጠንቀቂያው ቀጥሎ ቀርቧል። ታሪኩን ተናገር፣ ታሪኩን አንብብ።

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ሐዋሪያው ጳውሎስ የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን እንዴት ነው ያገለገለው?
2. መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስን ያስጠነቀቀው ምን ነበር? ጳውሎስ ለዚህ ምን ምላሽ ሰጠ? ለጳውሎስ እጅግ በጣም አስፈላጊ የነበረው ምንድነው? ቁ፣24

3. ለአንተ በጣም አስፈላጊ የሚሆነው ምንድነው፡- ወደ ሕይወት የምታስገባው (ማለትም ወንጌልን መመስከርህ) ነው ወይስ ከሕይወት የምታገኘው (ማለትም መስክረህ የምታሳምናቸው ነፍሳት)?
4. ሐዋሪያው ጳውሎስ የሚሰጣቸው ማስጠንቀቂያዎች ምንድናቸው? ቁ፣28, 29 እና 30 ያለው ክፍል ዛሬ እኛን ይመለከተናል ወይ?
5. የጳውሎስንና የኤፌሶን ቤተክርስቲያን ግንኙነት ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?
6. እግዚአብሔር ዛሬ ምን ያስተምርሃል?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ፀጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደከንቱ ነገር እቆጥራለሁ። (ሐዋ፡20፡24)*

<u>*ሰላሣ ሰባተኛ ሣምንት* ፣ *በድፍረት መመስከር*፣ *ሐዋ*፣22፡1-22</u>

*<u>መግቢያ</u>*፡- ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለሰ በኋላ አይሁድ ሊገድሉት ፈለጉ። አይሁድ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ስለጮኹ የሮማ ወታደሮች ጳውሎስን ያዙት። ጳውሎስ ለሕዝቡ ንግግር ለማድረግ ፈቃድ ጠየቀ። እሱ ያደረገው ንግግር በዚህ ክፍል ቀርቧል።
ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎችን በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ</u>

1. ጳውሎስ የጥንቷን ቤተክርስቲያን እንዴት ነው ያሳድድ የነበረው?
2. ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ ሳለ ምን ሆነ?
3. ኢየሱስ ምን አለው?
4. አናኒያ ለጳውሎስ ምን አለ?
5. ጌታ ስለ ኢየሩሳሌም ለጳውሎስ ምን ነገረው?
6. ጳውሎስ ዬት እንዲሄድ ነው ኢየሱስ የፈለገው?
7. ቀጥሎ ምን ሆነ?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ጳውሎስ እንዴት እንደተለወጠ ሐዋ፣9 ላይ አጥንተናል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ዝርዝር ሁኔታውን እንማራለን። በዚህ ክፍል የምትማረው አዲስ ነገር ምንድነው?
2. እግዚአብሔር ለጳውሎስ ዓላማ ነበረው። ሐዋ፣9፡15, 16 እና 22፡10 እና ቁ፣21 እንደገና አንብብ። እግዚአብሔር ለእሱ ያለው ዓላማው ምን ነበር?
3. ጳውሎስ ብዙ ስድብ፣ግሪፋትና ስደት ተቀበለ። በደረሰበት መከራ ሁሉ ሲያልፍ የረዳው ምን ነበር?
4. በችግር ጊዜ እንዲረዳህ ከዚህ ታሪክ ምን ተምረሃል?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ፀጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደከንቱ ነገር እቆጥራለሁ። (ሐዋ፡20፡24)*

<u>*ሰላሣ ስምንተኛ ሣምንት* ፣*ለምስክርነት መታዘዝ*፣*ሐዋ*፣26፡1-29</u>

*<u>መግቢያ፡-</u> ንጉሥ አግሪጳ ሊያየው ሲመጣ* ጳውሎስ በእሥር ቤት ለብዙ ጊዜ ቆየ። ጳውሎስ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለ ኢየሱስና ለአሕዛብ ያለውን ፍቅሩን ለሌሎች ይናገር ነበር። ታሪኩ ከዚህ በታች ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ጳውሎስ ወንጌልን እንዲመሰክር ኢየሱስ ጠራው። ይህ ጥሪ የሕይወት ዘመን ጥሪ ነበር። ካመንክ ይህ መንፈስ በአንተም ውስጥ ይሠራል። ፍርሃት ብኖርብህም አፍህን ለመክፈት ፈቃደኛ ነህ?
2. ንጉሡ ንስሐ አይገባም። ስለ እግዚአብሔር ድርሻና ስለ እኛ ድርሻ ምን እንማራለን?
3. ከዚህ ታሪክ የበለጠውን ልብህን የሚነካው የትኛው ክፍል ነው?
4. ቁ፣18 አንብብ። ይህ ምን ያስተምርሃል? ለሚጠፉ ነፍሳት ለመፀለይ ይህ ወሳኝ ክፍል ነው:: አሁን ለሚጠፉ ነፍሳት ፀልዩ።

*<u>የቃል ጥናት፦</u> ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ፀጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደከንቱ ነገር እቆጥራለሁ። (ሐዋ፡20፡24)*

<u>ሰላሣ ዘጠነኛ ሣምንት ፣ ጳውሎስ በሮሜ የሰበከው ስብከት፣ሐዋ፣28፡16-31</u>

*<u>መግቢያ፦</u>* ሐዋሪያው ጳውሎስ እሥር ቤት ሆኖ ለቤተክርስቲያናት ደብዳቤ ፃፈ። ለአይሁድም ስለ ኢየሱስ ይነግራቸው ነበር። ታሪኩ ቀጥሎ ቀርቧል።

ታሪኩን ተናገር፣ታሪኩን አንብብ።

<u>የሚከተሉትንና ሌሎችን ጥያቄዎች በመጠየቅ ታሪኩን የበለጠ ግልጽ አድርግ።</u>

1. ከጳውሎስ ጋር ለመነጋገር የመጣው ማን ነበር?
2. ጳውሎስ ስለመታሰሩ ለአይሁድ መሪዎች ምን አለ?
3. ጳውሎስ ለምን በሰንሰለት ታሰረ?
4. ጳውሎስ ስለኢየሱስ ነግሮአቸው ሊያሳምናቸው ሲሞክር ምን ሆነ?
5. ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ አይሁድ ምን አለ?
6. ነቢዩ ኢሳይያስ ወንጌልን ማን እንደሚሰማ ነው የተናገረው?

<u>የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ሐዋሪያው ጳውሎስ በገባበት ከተማ ሁሉ በመጀመሪያ ስለኢየሱስ የሚነግረው ለማን ነበር? ይህንን እርሱ ለምን ያደረገ ይመስልሃል?
2. ጳውሎስ ለአይሁድ መዳን ትኩረት እንደሰጠ እንማራለን። ከዚህ ምን እንማራለን?
3. ጳውሎስ ወደ ሮም ለመሄድ እንዴት እንዳቀደ ተወያዩ። ጳውሎስ ወደ ሮም እንዲሄድ ይህን ሃሳብ በልቡ ያስቀመጠው እግዚአብሔር ነው ትላለህ? ከዚህ ሁሉ ምን ትማራለህ?
4. ቁ፣30 እና 31 እንደገና አንብብ። ወንጌልን ስለመመስከር ምን ትማራለህ?

*<u>የቃል ጥናት፦</u> ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ፀጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደከንቱ ነገር እቆጥራለሁ። (ሐዋ፡20፡24)*

<u>አርባኛ ሣምንት ፣ ቤተክርስቲያን ምንድናት?</u>

*<u>መግቢያ፦</u>* እስካሁን ድረስ በነበረን ጊዜ ስለ ጥንቷ ቤተክረስቲያን ስናጠና ቆይተናል። በዚህ ሣምንት ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ባሕሪያትና ተግባር እንማራለን።

<u>የቤተክርስቲያን ትርጉም፦</u>

- ቤተክርስቲያን በውጭ የሚታይ ህንፃ አይደለችም፡፡
- ቤተክርስቲያን በሕብረት የሚኖሩ ሰዎች ክምችት ናት፡፡
- ቤተክርስቲያን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ስብስብ ናት፡፡

1. እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ‹‹የተጠሩ ሰዎች ክምችት›› የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ ይህ ላንተ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?
2. የቤተክርስቲያን ዓላማ ምንድነው?
3. በዚህ ባጠናቀቅነው ዓመት ስለ ቤተክርስቲያን ምን ተምረሃል?
4. ከዚህ ጥናት የተነሣ  በሕይወትህ እንዴት ለውጥ መጣ?

*<u>የቃል ጥናት፡-</u> ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ፀጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደከንቱ ነገር እቆጥራለሁ፡፡ (ሐዋ፡20፡24)*

*<u>የመጨመረሻው ክፍል አንድ</u>*

*<u>ምስክርነት ማዘጋጀት</u>*

1ጴጥ፣3፡15 አንብቡ፡፡ ጳውሎስ በመጀመሪያ ምን ይነግረናል? ክርስቶስን ጌታችን እንድናደርግ ይጽፍልናል፡፡ ወንጌልን መመስከር ጌታ ለሆነው ክርስቶስ መታዘዝ ነው፡፡ ሁለተኛ ምስክርነታችንን ለመስጠት ለምናገኘው አጋጣሚ ሁሉ ዝግጁ ሆነን መጠበቅ አለብን፡፡ ምስክርነታችን ያለንን ተስፋ ያብራራል፡፡ ምስክርነታችንን በትህትናና በአክብሮት መስጠት አለብን፡፡ ኢየሱስ ሳምራቷን ሴት ውሃ ዳር ባገኛት ጊዜ፡- ‹‹ለአንቺ ስለ እግዚአብሔር እናገራለሁ፣አንቺ ሴተኛ አዳሪ ነሽ›› አላለም፡፡ በመጀመሪያ ስለ ውሃ ነው የተናገረው፡፡ ከኢየሱስ ድርጊት መማር እንችላለን፡፡

ምስክርነትህን ለማቀናጀት የሚከተሉትን ሦስት ነጥቦች አስብ፡፡ እነዚህ ምስክርነትህን እንድታዘጋጅ ይረዱሃል፡፡

1. ጌታን ከመቀበሌ በፊት የነበረኝ ሕይወት
   ሀ. በምስክርነትህ ስለሐጢአት አካትት፡፡ ለምሳሌ፡-‹‹አሥርቱን ትዕዛዛት እስከማይ ድረስ ሐጢአት ምን እንደሆነ አይገባኝም ነበር…›› ወይም እንድህ ማለት ትችላለህ፡- ‹‹በሕይወቴ ከእግዚአብሔር ውጭ እጓዝ ነበር፡፡››
   ለ. እግዚአብሔር የምትኖረውን ኑሮ ሁሉ እንደሚያውቅ አብራራ፡፡ ከእግዚአብሔር ሊሰወር የሚችል  ምንም ነገር እንደሌለና በሀሳባችን የምንሰራውን ሐጢአት እንኳን ሳይቀር እንደሚያውቅ አብራራ፡፡ የምንናገራቸውን ቃላት ሁሉ እግዚአብሔር ይሰማል፡፡
   ሐ. ሊመጣ ስላለው ፍርድ አብራራ፡፡ ሐጢአቴ ከፃድቁ አምላኬ ለየኝ፡፡ እግዚአብሔር ዓለሙን በሙሉ ይፈርዳል፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ሁላችንም እንሞታለን፣ በእግዚአብሔርም የፍርድ ወንበር ፊት እንቀርባለን፡፡
   መ. ‹‹ጥፋተኛነትና ብቸኝነት ይሰማኝ ነበር›› በል፡፡
2. ጌታን እንዴት እንደተቀበልክ አብራራ፡፡
   ሀ. ስለ መስቀሉ፣ስለንስሐና፣ስለ እምነት ተናገር፡፡
   ለ. ‹‹ኢየሱስ ለምን እንደሞተ ገባኝ፡፡ ሐጢአቴን በሙሉ በቀራኒዮ መስቀሉ ደመሰሰው፡፡›› በል፡፡
   ሐ. ‹‹እግዚአብሔር ይቅር እንዳለኝና የዘላለምን ሕይወት እንደሰጠኝ እንድረዳ ዓይኖቼን ከፈተልኝ›› በል፡፡

መ. ‹‹ኢየሱስ ለእኔ ሞቶ ነበር፡፡ አሁን ግን ሕያው እንደሆነ አምኛለሁ፡፡ እርሱ ሕይወት እንደሚሰጠኝ አምናለሁ›› በል፡፡

3. ጌታን ከተቀበልኩ በኂላ ያለኝ ሕይወት
   ሀ. ጌታ በሕይወትህ ያመጣውን ለውጥና አሁን አዲስ ሰው መሆንህን አብራራ፡፡
   ለ. ‹‹አሁን መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ደግሞም በውስጡ ያሉትን እውነቶችን እረዳለሁ›› በል፡፡
   ሐ. አሁን አዲስ ልብ ስላለኝ ለጌታ እታዘዛለሁ፡፡
   መ. አሁን እንዴት መኖር እንዳለብኝ የሚያስተምረኝና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሃይል የሚሰጠኝ መንፈስ ቅዱስ አለኝ፡፡
   ሠ. አሁን በእግዚአብሔር ሰላም አለኝ፡፡
   ረ. አሁን ሕይወቴን እግዚአብሔር እንዲቆጣጠረውና እንዲረዳኝ ለእርሱ ሰጥቻለሁ፡፡

<u>የመጨረሻው ክፍል ሁለት</u>

<u>ስለኢየሱስ ለመናገር መንደርደሪያ የሚሆኑ ጥያቄዎች</u>

ብዙ ሰዎች ስለ መንፈሳዊ ነገሮች መነጋገር ደስ ይላቸዋል፡፡ እዚህ ጋ ቁልፉ መጀመሪያ እነሱ የሚሉትን መስማት ነው፡፡ ከዚያም እነዚህን ጥያቄዎችን ተጠቅመህ የንግግሩን አቅጣጫ ቀይረህ የራስህን እምነት ማካፈል ትችላለህ፡፡

1. በሕይወትህ(ሽ) ምን እየሆነ ነው? እነዚህ ሁኔታዎች ወደ እግዚአብሔር እንድትመለከት(ቺ) እንዴት አደረጉህ(ሽ)?
2. ስለ እግዚአብሔር ያለህ(ሽ) ሀሳብ ምንድነው?
3. ወደ ቤተክርስቲያን ትሄዳለህ (ትሄጂያለሽ)? ከሄድክ(ሽ) ለምን? ካልሄድክ(ሽ)ስ ለምን?
4. እምነትና መንፈሳዊ እሴቶች (እውነቶች) ለሥራህ(ሽ)፣ለትዳርህ(ሽ)ና ለሚደርስብህ(ሽ) ችግር እርዳታ ያመጣሉ ብለህ(ሽ) ታስባለህ(ሽ)?
5. ለተወሰኑ ጊዜአት አብረን ቆይተናል፡፡ ነገር ግን በሕይወቴ ስላየሁት አንድ በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገር አልነገርኩህም (አልነገረኩሽም)፡፡ እሱን አሁን ልንገርህ(ሽ)?
6. አንድ ሰው እንዴት ክርስቲያን ይሆናል ብለህ(ሽ) ታስባለህ(ሽ)?
7. በሶዶ ከተማ ብዙ ሰው ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳል፡፡ አንድን ሰው እውነተኛ ክርስቲያን የሚያደርገው ምንድነው?
8. በምሽት ምን ትሆናለህ(ትሆኚያለሽ)? ትጨነቃለህ(ትጨነቂያለሽ)? ወይስ ምን ትሆናለህ(ትሆኚያለሽ)? ከክርስቶስ ጋር ሕብረት ካደረክ(ሽ) ሰላም ሊኖርህ(ሽ) ይችላል፡፡ ስለዚህ ነገር ላብራራልህ(ሽ)?
9. ዛሬ ማታ ብትሞት(ቺ) ምን እንደምትሆን ታውቃለህ(ታውቂያለሽ)? ወደ ሰማይ ወይስ ወደ ገሃኔም ትሄዳለህ(ትሄጂያለሽ)?
10. እኔን ጥሩ አባት፣እናት ወይም ጥሩ ሠራተኛ እንድሆን ያደረገኝን እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ልንገርህ(ሽ)?
11. ስለ እግዚአብሔር ጥያቄ አለህ(ሽ)?
12. ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝህ(ሽ) አድርገህ(ሽ) ተቀብለሃል(ሻል)? እኔ ጌታን እንዴት እንደተቀበልኩ ልንገርህ(ሽ)?